**Hallo**
**Basel-Stadt**

Kanton Basel-Stadt

# ገንዘብ እና ታክስ

የባንክ ሒሳብ/ የግብይት ክፍያዎች

ታክስ

ዕዳ

በጥቂት ገንዘብ መኖር

# የባንክ ሒሳብ/ የግብይት ክፍያዎች

**ገንዘብ የሚከፈለው እና ሒሳቦች መክፈል የሚገባው ሰው የባንክ ወይም የፖስታ ቤት የባንክ ሂሳብ ያስፈልገዋል። ለግገር ዴቢት ወይም ክሬዲት ካርዶች በብዛት ጥቅም ላይ ውለዋል በጣም ተስፋፍተዋል።**

## የባንክ ሒሳብ

በስዊዘርላንድ ነዋሪ የሆነ እያንዳንዱ ሰው የባንክ ሂሳብ አለው።ተቀጣሪዎች በአጠቃላይ ደመወዛቸው በባንክ ሒሳባቸው ብቻ ነው የሚከፈላቸው። በብዙ የሚቆጠሩ ባንኮች እና የፖስታ ቤት ባንኮች ለግለሰቦች የባንክ አገልግሎት ይሰጣሉ። የባንክ ሒሳብ መክፈት ብዙውን ጊዜ ነፃ ነው። ይሁን እንጂ በተለያዩ አካባቢዎች ክፍያዎች አሉ።. ጀምሮ ክፍያዎች፣ ወለዶች፣ እና የተለያዩ አገልግሎቶች አንደየ ባንኩ ክፍያ ዋጋው ይለያያል። ስለዚህ ማወዳደር ይጠቅማል። በማንኛውም አጋጣሚ ባንክ ለመክፈት ፓስፖርት ወይም ሌላ መታወቂያ ያስፈልጋል።

## ዴቢት ካርድ / ክሬዲት ካርድ

የባንክ ሒሳብ ያለው ሰው ገንዘብ ለመቀበል የባንክ ካርድ ማግኘት ይኖርበታል። ይህ የሚሰራው በራሱ ባንክ ብቻ ነው። ባንኮቹ ወይም የፖስታ ባንኮቹ ግን የዴቢት ካርዶችን (ለምሳሌ Maestro) ያቀርባሉ፣ በዚህም ከሁሉም የባንክ ሂሳቦች እና ከአብዛኞቹ ሀገራት ገንዘብ ማውጣት ይችላሉ እናም በብዙ የገበያ ሱቆች መጠቀም ይቻላል። እነዚህ ካርዶች በውጭ አገርም ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።. እንደ ካርዱ ዓይነት የተለያየ ዋጋ ግብር ያስከፍላል። ክሬዲት ካርዶች ለማግኘት በተለያዩ አቅራቢ ባንኮች ማመልከት ይቻላል። አገልግሎት አሰጣጡ እና የክፍያ ግብሩ ከባንክ ባንክ ይለያያል፣ ስለዚህ ማወዳደር ይጠቅማል። በዴቢት ወይም ክሬዲት ካርድ ክፍያ መፈጸም በሁሉም ቦታ ተስፋፍቷል።

## ሂሳቦችን መክፈል

ብዙውን ጊዜ የሒሳብ ክፍያዎች (Rechnungen) በፖስታ ወይም በኢሜይል በመክፍያ ደረሰኝ ዝርዝር ይላካሉ። ሊታሰብባቸው የሚገቡ ሦስት የአከፋፈል አማራጮች አሉ፡-

- ኢ-ባንኪንግ፡ በኢንተርኔት በኩል የሚደረጉ ግብይቶችን ክፍያዎች በጣም የተስፋፉ እና አስተማማኝ ናቸው።
- በባንክ መክፍያ መስኮት፡ በመክፍያ ደረሰኝ በፖስታ ቤት በጥሬ ገንዘብ ክፍያ መክፈል ይቻላል። የፖስታ ባንክ ያለው ሰው ገንዘቡን በቀጥታ ከባንክ ሒሳቡ መክፈልና ማስተላለፍ ይቻላል። የባንክ ደንበኞች ከባንክ ክፍያዎችን በባንክ መክፍያ መስኮት ክፍያውን መፈጸም ይችላሉ።
- በፖስታ፡- ገንዘብን ለማስተላለፍ በፖስታ አድርጎ ለባንክ ወይም ለፖስታ ቤት መላክ ይቻላል። እባክዎ ተጨማሪ መረጃው ለማግኘት ባንክ ቤት ወይም የፖስታ ቤት ባንክ ቤት ይጠይቁ።

ለሚደጋገሙ ሒሳቦች የአከፋፈል አማራጮች፡-

- የቀጥታ ክፍያ ሂደት Load Ledger Vendor (LSV) አላላክ ምቾት ይሰጣል።ምክንያቱም የሒሳብ ክፍያው ወድያውኑ በፍጥነት ከባንክ ሒሳብ ላይ ይወስዳል። ስለ ሁኔታው ተጨማሪ መረጃው ለማግኘት ባንክ ቤት ወይም የፖስታ ባንክ ቤት ይጠይቁ።
- ሂሳቡ ከፍ ያለ ከሆነ (ለምሳሌ ያህል የኪራይ ክፍያ) በባንክ ወይም በፖስታ ባንክ ቤት ገንዘቡ በግዜው ባንኩ እንዲያስተላልፍ ዘለቄታው ውል (Dauerauftrag) መፈጸም ይቻላል።

ክፍያዎች ሁልግዜ የክፍያ የጊዜ ገደብ አላቸው።መጠየቅ ይችላሉ። ይህ የክፍያ የጊዜ ገደብ ክፍያው ሳይፈጸም ገደቡ ቢያልፍ፣ ጣጣ ሊያመጣ ይችላል። ገንዘቡን የግድ ከነቅጣቱ ማስከፈል (Betreibung) ይቻላል።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/geld-und-steuern/konto--zahlungsverkehr

# ታክስ

የቀረጥ ክምችት በስዊዘርላንድ እንደምትኖርበት አካባቢ ይለያያል። ለግለሰቦች አስፈላጊ የሆኑ ታክሶች የገቢ፣ የንብረት እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ናቸው።

## የታክስ ስርዓት

በስዊዘርላንድ፣ በፌደራል፣ በካንቶኖች፣ በኮምዩን ደረጃ እና ሕዝባዊ በሕግ መብት ያላቸው ሃይማኖታዊ ማህበረሰቦች_ታክስ (Steuern) ያስከፍላሉ። ቀጥታዊ ታክስ እና ቀጥታዊ ያልሆንኑ የታክስ ዓይነቶችን መለየት ያስፈልጋል። ቀጥታዊ ከሆኑ የታክስ ዓይነቶች መካከል በተለይም የተጨማሪ እሴት፣ የገቢ እና የንብረት ታክሶች በተጨማሪም የትምባሆ ታክስ ወይም የነዳጅ ታክሶች ናቸው። እነዚህ ታክሶች በዕቃዎቹ ዋጋ ውስጥ ተካተዋል። ታክሶችን በሚመለከት የካንቶኖችና የኮምዩኖች ሃላፊነት ስለሆነ ቀጥታዊ የሆኑ የታክስ ዓይነቶች እንደ መኖሪያው አካባቢ ከፍታኝ ልዩነት አላቸው። ባለትዳሮች በአንድ ላይ ነው ታክስ የሚከፍሉት።

## ተቀናሽ ታክስ

አዲስ የመጡ የውጭ ዜጎች የገቢ ታክስ በቀጥታ ከደሞዛቸው ይቆረጣል። (ተቀናሽ ታክስ፣ Quellensteuer).ነው። ምዝገባ የሚከናወነው ለሠራተኞች በአሠሪው ነው።

- የታክሱ መጠኑ በገቢ፣ በጋብቻ ሁኔታ (ያላገባ፣ ባለትዳር፣ የተፋታ) እና በልጆች ብዛት ላይ የተመሰረተ ነው። ለውጦች ካሉ ወዲያውኑ ሪፖርት መደረግ አለባቸው።
- ከተቀናሽ ታክሶች በተጨማሪ የተለያዩ ሌሎች ተቀናሽ ታክሶች ለምሳሌ ለ 3 ኛ ምሰሶ 3. Säule፣ የዕዳ ወለድ፣ ከፍተኛ የህክምና ወጪዎች፣ ወዘተ
- ንብረቶች ካሉዎት፣ ማስታወቅ እና ቀረጡን ለብቻው ለይተው መክፈል አለቦት።
- በዓመት ከ120,000 ፍራንክ ገቢ በላይ ያለው ሰው፣ በየዓመቱ ታክስ ማወራረድ አለበት (መደበኛ ታክስ)።
- የስዊዝ ፓስፖርት ወይም ሲ የመኖሪያ ፍቃድ ካለው የትዳር ጓደኛ ጋር ከተጋቡ በየዓመቱ ታክስ ማወራረድ (መደበኛ ግብር) አለበት።

የካንቶናል ታክስ አስተዳደር ጽ/ቤት (Kantonale Steuerverwaltung) ስለ ተቀናሽ ታክስ ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል። የካንቶናል ታክስ አስተዳደር ጽ/ቤት ስለ ንብረቶች ቀረጥ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል።

## መደበኛ ግብር

የስዊዝ ፓስፖርት ወይም የ C የመኖሪያ ፍቃድ ያላቸው ሰዎች በመደበኛነት ቀረጥ ይከፍላሉ (ordentliche Besteuerung) ።ግብሩ ከደሞዝዎ አይቀነስም። በየዓመቱ ታክስ ማወራረድ እና ግብሩን በክፍያ መጠየቂያ መክፈል አለቦት። ታክስ ማወራረድም በኦን ላይን በመስመር ላይ ሊሞሉ ይችላሉ። የቅድሚያ ክፍያ (Vorauszahlung) መክፈል ይመከራል።የሚጠበቀው የታክስ መጠን የታክስ ስሌት ማስያ (Steuerrechner) በመጠቀም ሊሰላ ይችላል።. ታክስ ማወራረጃ ቅጹን መሙላት ለስዊዘርላንድ ዜጎችም ጭምር ውስብስብጋ አዳጋች ነው። ስለዚህ በተለይ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሞሉ ታክስ ለማወራረድ የሚያግዞት ቢኖር ይመረጣል።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/geld-und-steuern/steuern

# ዕዳ

ሒሳቦችን በወቅቱ ያልከፈለ ሰው፣ ከባድ መዘዝ ሊያስከትልበት ይችላል።. የፋይናንስ ችግር በሚያጋጥምዎት ግዜ የዕዳ አማካሪ ማዕከላት ድጋፍ ይሰጥዎታል።

## ማስጠንቀቂያ እና ዕዳ ማስፈጸሚያ

የሒሳብ ክፍያ በሰዓቱ ካልከፈሉ፣ በመደበኛነት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ማስጠንቀቂያ (Mahnung). ይደርስዎታል። ሆኖም አበዳሪዎች በማንኛውም ጊዜ የዕዳ ማስፈጸም (Betreibung) የማስጀመር ስልጣን አላቸው። በዚህ ግዜ ተበዳሪው ከሚመለከተው የዕዳ ማስፈጸሚያ ቢሮ (Betreibungsamt). የክፍያ ትዕዛዝ ይደርሰዋል።. ለአሰራር ሂደቱ ተጨማሪ ያስከፍላል። የዕዳ ማስፈጸሚያው ህጋዊ አይደለም ብሎ የሚያምን ማንኛውም ሰው፣ ህጋዊ ፕሮፖዛል (Rechtsvorschlag) ኃላፊነት ካለው የዕዳ ሰብሳቢ ጽሕፈት ቤት በማቅረብ መቃወም ይችላል። ማሳሰቢያ፡ ዕዳ አስፈጻሚው ደሞዝ ወይም ውድ ዕቃዎችን እንደ መያዣ አድርጎ ሊይዝ ይችላል። በተጨማሪም የዕዳ አስፈጻሚው በዕዳ ማስፈጸሚያ መዝገብ (Betreibungsregister) ውስጥ (ከፍለው እንኳን ቢሆንም) መዝግበው ይይዛሉ።. ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ አፓርታማ በሚፈልጉበት ጊዜ ችግር ሊፈጥርብዎት ይችላል።.

## ዕዳ

የገንዘብ ችግር ወይም ዕዳዎች ካሉብዎት የዕዳ አማካሪ ማዕከልን (Schuldenberatungsstelle) ማነጋገር ይችላሉ። እዚያም ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። ባለሙያዎቹ ከምክር ፈላጊዎች ጋር አንድ ላይ በመሆን ሁኔታውን ይመለከታሉ እና መፍትሔዎችን ይፈልጋሉ። የካሪታስ ድርጅት ስም-አልባ ምክር በስልክ ይሰጣል።- “SOS ዕዳ” የምክር አገልግሎት የስልክ መስመር፣ ስልክ 0800 708 708 (ከክፍያ ነፃ) ነው። እንደስፈላጊነቱ ወደ ሌላ ቦታ ይመሩዎታል።. ከPlusminus የምክር አገልግሎት ማዕከል እርዳታ እና ጠቃሚ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/geld-und-steuern/schulden

# በጥቂት ገንዘብ መኖር

የስዊዘርላንድ ሕይወት በአንጻራዊነት ውድ ነው። ስለዚህ ያገለገሉ አንዳንድ ዕቃዎችን መግዛት ሊጥቅም ይችላል። ገንዘብ የእጥረት ያለበት ሰው፣ በልዩ ቅናሽ ሱቆች ውስጥ በርካሽ መግዛት ይችላል።

## ያገለገሉ ዕቃዎች

በስዊዘርላንድ ውስጥ ብዙ የቁጠባ መደብሮች (Brockenhäuser) አሉ። ያገለገሉ ዕቃዎች እዚያ በጣም በርካሽ መግዛት ይችላል። ነጋዴ ያልሆኑ ግለሰቦች ያገለገሉ ዕቃዎችን ለሽያጭ በልዩ ገበያዎች ያቀርባሉ። ምሳሌዎች ተንቀሳቃሽ ገበያዎች (Flohmärkte)፣ የልብስ ልውውጥ፣ የበረዶ መንሸራተቻዎች፣ ወዘተ በቅናሽ ይሸጣሉ። ኢንተርኔት ፖርታሎች ያገለገሉ ዕቃዎችን ለመግዛት እና ለመሸጥም በጣም ተወዳጅ ናቸው።

## ስፖርት / ባህል / ትምህርት

በKulturlegi መታወቂያ ካርድ፣ በቂ ገንዘብ የሌላቸው ሰዎች ለመዝናኛ፣ ለስፖርት፣ ለባህላዊ እና ትምህርታዊ ዝግጅቶች ቅናሽ ያገኛሉ። ካርዱን ለማግኘት በካሪታስ ማመልከት ይቻላል። ካሪታስ መረጃ ይሰጣል እናም በመቀጠልም የKulturlegi መታወቂያ ካርድ ለማግኘት መብት እንዳለህ ያጣራል። እንደዚሁም በFamilienpass፣ በFamilienpassPlus ወይም colorkey ለብዙ ዝግጅቶች ቅናሾችን ያገኛሉ።

## የካሪታስ ሱቅ

ጥቂት ገንዘብ ያላቸው ሰዎች በካሪታስ ሱቆች (Caritas Markt) ውስጥ ምግቦች እና የዕለት ተዕለት ምርቶችን በጣም በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛት ይችላሉ። ለዚህ ልዩ ካርድ ያስፈልግዎታል፣ ይህንንም ለማግኘት ካሪታስ ማመልከት አለብዎት። ካሪታስ መረጃ ይሰጥዎታል እና ካርዱን የማግኘት መብት እንዳለዎት ያጣራል። ባዝል ውስጥ አንድ የካሪታስ ሱቅ አለ።

## የመንግስት ድጋፍ

ለመኖር በጣም አነስተኛ ገንዘብ ያለው ሰው፣ በብዙ መስክ የመንግስት ድጋፍ የማግኘት መብት አለው። ለምሳሌ፣ ቅናሽ የጤና ኢንሹራንስ ፕሬምየም ወይም ለሥልጠና ስኮላርሺፕ ማመልከት ይቻላል። በተወሰኑ የህይወት ሁኔታዎች ውስጥ ከማህበራዊ የድህነት ኢንሹራንስ ወይም ከማህበራዊ እርዳታ ገንዘብ ማግኘት ይቻላል። በቂ ገንዘብ የሌላቸው ቤተሰቦች በተወሰኑ ሁኔታዎች መስፈርቱን ካሟሉ የቤተሰብ የኪራይ ድጎማ (Familienmietzinsbeiträge). ማመልከት ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/geld-und-steuern/leben-mit-wenig-geld